ሐዋርያ፥ 12፥ ቅጽ 2 ቁ.

## ርዕስ አንቀጽ

# የማን ትግል፥ ለማን ሥልጣን?!

ሰው ለተፈጥሮ ችሎታው  በምድር ላይ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ልዩ ሃይል ነው። ይህ ፍጡር ከእንስሳት ዓለም በባህርይው፥ በፍላጎቱና በአድራጎቱ ልቆ ምድርን መቆጣጠር ከጀመረበት ዘመነ ህልቅ ጀምሮ የሚታወቀው፥ ለመብቶቹና ለፍጆታው ሲል በማያቋርጥ የትግል ሂደት ውስጥ ማለፉም ነው። ይህ ማህበራዊ ግንኙነትንና ተፈጥሮን እየገራ የሚያስገብር ልዩ ሃይል - ሰው- በፍጥረተ ባህርይው ጥሮ ግሮ መኖር ይችል ዘንድና ፍላጎቱቹን ለማሟላት፥ በነፃው ተፈጥሮ ውስጥ በሚገኙ የተወሰኑ ቁጥብ ሃብቶችና በማህበራዊ ግንኙነቶች አመካይነት በተፈጠሩ ሳንካዎች ላይ ያደረጋቸውና እያካሄዳቸው የሚገኙት ዘርፈ ብዙ ትግሎቹ ምንጊዜም ወደፊት አራምደውታል፤ የጥበብና የሥልጣኔ ጌታም አድርገውታል።

ምንም እንኳ ተፈጥሯዊውና ማህበራዊው የለውጥ እውንታ በሂደቱ አዝጋሚና ብዙ ባህሪዎች ያሉት ቢሆንም፥ ሰዎች በሚፈጥሩት ውስብስብ ማህበራዊ ግንኙነትና እርስ በርስ ፍትጊያ ግፊት የሚበቅሉ ግለሰቦች፥ በማህበራዊው የሹም ሽረት ሂደትና ፍጻሜው ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አላቸው። በየህብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ በንቃታቸውም ሆነ በጡንቻቸው ፈርጠም ያሉ ግለሰቦች፥ እጅግ ብዙ የሆኑ ደካማ አምሳዮቻቸውን መብቶችና ንብረቶቻቸውን እየገፈፉ ኖረዋል። ከሰው ልጅ ጥንታዊ የአደን ዘመን በሁዋላ እያደገ በመጣው ህብረተሰብ ውስጥ፥ በየደረጃው የባሪያ ጌቶችንና ቆየት ብሎም ብዙሃኑን ከተፈጠረበት መሬት ነጥለው እንደከብት ከነዱ የመሬት ከበርቴዎች እስከ ዘመናችን ነብስ በላ የኑዋይ ጌቶች ድረስ ያለውን የግለሰቦች ሚና ታሪክ መጥቀስ ይቻላል።  ይህን የተዛባ ማህበራዊ  ግንኙነት ለማስተካከል አብዛኛው ከጥቂቶች ጋር ያደረገው ያላሰለሰ የግብግብ ታሪክ ትውፍሲትም ለዛሬው ትውልድ በአያሌ ዘመናት ትግል ተባዝቶና ተዳውሮ ተላልፎለታል።

በየሀገሮችና በየማህበረሰቡ የሚካሄዱትን የዘመናችንን የማህበራዊ ግንኙነት ለውጥ ትግሎች ካለፉት የተለያዩ የሥርዓት ሹም ሽር ክንውኖች ልዩ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር፥ ዛሬ ሰለጠነ በተባለው ዘመን ላይ ህብረተሰቡ ኑሮውንና መብቶቹን ለማሻሻል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ የመሪነት ሚናውን ለመጫዎት ከመካከሉ ብቅ የሚሉት ግለሰቦች፥ የምልዓተ ሕዝቡን ጥያቄ ተከናንበው በሕዝቡ ስም ከመራራ ትግሉ ጀርባ በሥልጣን እርካብ ላይ ለመንጠላጠል የሚያፈሱት የአዞ እምባ ነው። የሰብአዊ መብትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች አስቦ ለሚያድረው የሰው ልጅ ትልቅ ጉዳዮቹ ናቸውና፥ የዛሬ ጮሌዎች በነዚህ ሕዝባዊ ጥያቄዎች ስም ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን አጭተው ለመሪነት በማቅረብ ያደረሱት በደል ቀላል አይደለም። ለዚህም፥ በሀገራችን በኢትዮጵያ ላለፉት በዛ ያሉ ዓመታት በየፖለቲካ ፓርቲዎች ምህዋር የሚሽከረከሩ የድርጅት አለቆች የፈጸሙትንና እያደረሱ ያለውን በደል ማጤኑ በቂ ነው።

ሕዝብ የመብትና የነጻነት ጥያቄዎችን አንስቶ በትግሉ ፍኖት በሚጓዝበት ወቅት፥ የፖለቲካውን መዘወር ጨብጠው ተሳፋሪውን ሕዝብ ህልፈታችን ከአንተ በፊት ትሆናለች የሚሉ አስመሳይ ደንገጡሮች በየደረጃው ክፉ ሽል ሆነው ተወልደዋል። እነዚህ አሳዊ ፖለቲከኞች ላጡ ለነጡ የፖለቲካ ነድያን “ሥልጣን የሕዝብ ነው!” የሚለውን መፈክር ቢያነሱም፥ ባነገቡት መፈክር አፎት ውስጥ የታጠቁት ስለት ለሥልጣን ይበቁ ዘንድ የሕዝቡን ክርና ማግ - አንድነቱንና ግንኙነቱን- መቁረጫ መበጠሻቸው በመሆኑ፥ መሠረታዊው ሕዝባዊ መፈክር የአባባላቸው አቃቂር ከመሆን አላለፈም። የሕዝብን የበላይነት እውን ለማድረግና የሀገርን ሉአላዊነት ለመጠበቅ ሲሉ እጅግ ብዙ ሰማእታት ታግለው በወደቁበት የትግል ጥርጊያ ላይ፥ የገቡትን ቃል ኪዳን ረስተው ተክለ-ሰውነቶቻቸውን የሚያሰማምሩ ግብዞች ብቅ እያሉ ከፍተኛ ጉዳት በየጊዜው አድርሰዋል። እነኝህን መሰል ቡክኖች መጨረሻቸው አይወድቁ ውድቅት፥ አይከስሩ የታሪክ ክስረት መሆኑን ግን፥ ነገ ከነገ ወዲያ በሕዝብ ትግል ክሳራ “አጅሬ” ለመባል ልባቸው የሚሻቅል ሁሉ ትምህርት ቢወስዱበት ምንኛ በተገባ ነበር። ዳሩ ግን ትምህርቱ አጥጋቢ አይደለ ይመስል በየጊዜው  ከመከሰቱ በላይ፥ በዚህ አይነቱ የታሪክ ሞት የሚሰናበቱት የሥልጣን ሰፍሳፎች ብቻ ሳይሆኑ እየቀደሙ ተፍ ተፍ በማለታቸው፥ የመሯቸውና ያታገሏቸው እየመሰላቸው እስከመጨረሻቸው አብረዋቸው የቆሙት

አንዳንድ የየድርጅቶቻቸው አባላትና ጨዋ የሕዝብ ወገኖች ጭምር ናቸው በዚህ አይነቱ የታሪክ ማቅ ተሸብልለው አብረው የሚቀበሩት።

በተራዘመው የኢትዮጵያ የብዙ ዓመታት የሥርዓት ለውጥ ትግል ውስጥ፥ እንደ እባብ መርዛም የሆኑ፥ እንደ አለት ለሕዝብ ልባቸው የጠጠረ ራስ ወዳድና ለሥልጣን ስግብግብ ግለሰቦች ባይኖሩ ኖሮ፥ ትግሉ ድሮ ገና ከግንቦት 1997ቱ ሕዝባዊ ትንግርት ክስተት በፊት በድል በተጠናቀቀ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር ትክክለኛ የፖለቲካና የመብት ጥያቄዎችን አንስቷል፤ በትግሉ ጎራም በያለበት ተሰልፎ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለመጭው ትውልድ ብሩህ ተስፋ ሲል በግንባር ቀደምትነት እየተዋደቀ መስዋእት ሆኗል። እዚህ ላይ፥ ታዲያ ለምን እስካሁን ለአስተማማኝ ድል አልበቃም የሚል ጥያቄ ማንሳት አግባብነት ይኖረዋል። ለጥያቄው መልስ ምንም እንኳ ብዙ ሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም፥ በዋናነት ግን የፖለቲካው አብሪ ነን የሚሉ ግለሰቦች የተጫወቱት አደናቃፊና መሠሪ ሚና እንዲህ በቀላሉ ይቅር የማይባል በደል መሆኑ ተዘግቦ ለታሪክ መተላለፈ ያለበት ጉዳይ ነው። አክብረውት የሚከበሩበትን፥ ጠቅመው የሚጠቀሙበትን የሕዝብ ተጋድሎና የሥልጣን ባለቤትነት ለራሳቸው የግል ጥቅማጥቅምና የዝነኝነት እሴት እያሰሉ፥ በቅድሚያ ግለ-ሰውነታቸውን ከተከበሩበት ማማ አውርደው እመቀመቅ ከመጣላቸው በላይ፥ ህልቆ መሳፍርት የሌለው መስዋእትነትና ድካም በተቸረው የሕዝብ ትግል ላይ ትቢያ ነስንሰዋል። 'የማን ትግል፥ ለማን ሥልጣን' ስንልም ለሕዝባዊ ትግሉ ወገናዊነታችን እየገለጽን፥ ሕዝብ በሕዝብ፥ ሕዝብ ለሕዝብ የሚዳኝበትንና የሚፈርድለትን አዲስ ሥርዓት በመመኘትና በመናፈቅ ነው። ወቅቱም የካቲት ነውና፥ ይኸውን ቃል ኪዳን በማደስ፥ ፍትህ ርትእ የሰፈነባት፥ ሉአላዊነቷና አንድነቷ የተጠበቀ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት ከሚታገለው ሕዝብና የሕዝብ ወገኖች ጎን እንቆማለን።